**ጉዳዩ:-** <u>**የAfrica Economic Outlook 2010 ሪፖርት ኢትዮጵያ በአጠቃላይ የብሄራዊ ምርት ዕድገት (GDP) በአፍሪካ ቀዳሚ መሆናን ስለመገለጹ**</u>

**የAfrica Economic Outlook 2010 ሪፖርት ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2009 እና በ2010-11 በአጠቃላይ የብሄራዊ ምርት ዕድገት ከአፍሪካ ቀዳሚ መሆኗን አመለከተ፡፡ የአፍሪካ ልማት ባንክ፣ የአፍሪካ የኢኮኖሚ ኮሚሽንና የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት (OECD) በጋራ ባወጡት የ2010 ዓመታዊ ሪፖርት ኢትዮጵያ በተጠቀሱት ጊዜያት አጠቃላይ ኢኮኖሚዋን በሁለት አሃዝ በማሣደግ በአፍሪካ ቀዳሚውን ስፍራ መያዟን አመላክቷል፡፡ በተጨማሪም ሪፖርቱ እ.ኤ.አ በ2009 እና በ2010-11 በአጠቃላይ የነፍስ ወከፍ የምርት ገቢ (per capita GDP) ከአፍሪካ የመጀመሪያ መሆኑን ገልጿል፡፡**

**ሪፖርቱ የምዕተ ዓመቱን ግቦችን በማስመልከት ባወጣው መረጃ ኢትዮጵያ ግቦቹን ከሚያሣኩት የአፍሪካ አገሮች ጎራ እንደምትሰለፍ ያመለክታል፡፡ ኢትዮጵያ ድህነትንና ረሃብን በመቀነስ፣ በትምህርት፣ በጤናና በሽታዎችን በመከላከል እያስመዘገበች ያለችው ውጤት እ.ኤ.አ. ከ2015 በፊት ቀድማ ግቦቹን እንደምታሣካ (early achiever)፣ እንዲሁም የሴቶች እኩልነት በማስፈንና የሕጻናትን ሞት በመቀነስ ረገድ በትክክለኛ ጎዳና እየተራመደች በመሆኑ በዚህ ረገድ የተቀመጡትን ግቦች እንደምታሳካ ሪፖርት ጠቁሟል፡፡ የአካባቢ ዘላቂ ልማት በማረጋገጥ ረገድ ብዙ መሠራት እንዳለበት አመልክቷል፡፡**

**የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እ.ኤ.አ ከ2003 ጀምሮ በሁለት አኃዝ በአስደናቂ ሁኔታ እያደገ መሆኑን የገለጸው ሪፖርት፣ መንግስት በወሠዳቸው ትክክለኛ የኢኮኖሚ ዕርምጃዎች የዋጋ ንረቱ ወደ አንድ አሃዝ መውረዱንና የውጭ ምንዛሬም መጨመሩን ያመለክታል፡፡**